# <u>ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?</u>

ቁጥር 7

የነፃነት ትርጉም ምንድነው ምስጢሩ
ሰው እንሰሳ ሲሆን በገዛ ሀገሩ
ወንዜ ተራራዬ ማለቱ ምንድነው
ጭቆናው ብዝበዛው ብሶቱ ካልገባው ?

ተው ስማኝ ሀገሬ ብሎ የዘመረው ያ ጀግና ትውልድ በመዘሙር ሳይወሰን ጭቆናና ብዝበዛን ለማስቆም ውድ ሕይወቱን ገብሯል:: በዚያው ጊዜ ደግሞ ባንዳውም ጠባቡም ፈልቶ ሀገርን በከፍተኛ ደረጃ ጎድቷል:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አይሎ ባለበት ሕዝብን በጠባብ ብሄረተኛነት ሊቃኙና ሀገርን ሊገነጣጥሉ የተነሱት ሁሉና ከአረመኔው አገዛዝ ጋር አብረውና ወግነውም ኢሕአፓንና የሕዝብን ትግል ለማውደም ደም ያፈሰሱትም ብቅ ብቅ ብለው ጥፋት አድርሰዋል :: ዛሬ አንዳንዶቹ ለስልጣን ሲበቁ፤ ሌሎች በተራቸው ተሰደው ግን አሁንም በኢሕአፓ ላይ ሲጨፍሩ፤ ሌሎች ደግሞ ካባ ቀይረው ታሪክ ደብቀው ተቃዋሚ ወይም ወያኔ ሆነው ሲውገረገሩ እያየን ነው:: ያ ትውልድ ግን የህይወት ዋጋ ከፍሎና ሀገሩን ሊያስከብር በጀግንነት ታግሎ አልፏል:: ደሙ ግን የፍትህ ያለ መጮሁ አልቀረም--ተው ስማኝ ሀገሬ!

ዛሬ ግን ይሉናል ያ ታሪክ ውሸት ነው
በከንቱ ነበረ ያ ደም የፈሰሰው ::

ለተወሰነ ጊዜ ሐሳዊ መሲሆች፤ የቅጥፈት ጳጳሶች፤ የውሸት ሼኮች ሀገርን ሊያጠቡና ሊያደነቁሩ ም ይችላሉ-- ይህ ግን መቼም ዘላቂ ሆኖ አያውቅም:: ጊዜን ፈጅታ ሀቅ ብቅ ትላላች፤ አቸናፊነቷንም ታረጋግጣለች:: ዋሾዎቹም ይጋለጡና የሀፍረት ማቅ ይለብሳሉ:: ያ ሞት ባይለመድም ማን ይፈራል ሞት ብሎ የተሰዋውን ትውልድ ዛሬ ስሙንና ታሪኩን ለማጥፋት በጣምራ የተነሱ ት ወያኔዎችና የደርግ ርዝራዥ ወንጀለኞች በጅምላ መወገዝ ያለባቸው ናቸው:: በትግል መሞት ህይወት ዳግም ትንሳዔ ልደት ብሎ ፋሺስቱን ደረግ ሲዋደቅ የተሰዋው ትውልድ አላዋቂ ሆኖ ወይም ደርግ በዚያ አስገራሚ ድንቁርናው ይል እንደነበረው " ሳያናይድ የተባለ አደንዛዥ ዕፅ" (!') ወስዶ ሳይሆን፤ ወይም ዛሬም ወያኔም ተጨምሮ እንደሚሉት የኢሕአፓ አመራር ሂድ ሙት ውደም ብሎ ማግዶት ሳይሆን ሀገሩንና ወገኑን በማፍቀሩና ሀገርም ሕዝብም ከጭቆና ሊላቀቁ የሚችሉት በትግልና በመስዋዕትነት መሆኑን በመረዳቱ ብቻ ነው:: ዛሬም ቢሆን ለነፃነትና መብትን ለማስከበር ሌላ መንገድ ከቶም የለም:: ለፍጅቱ ተጠያቂው ሰለባውና የተገደለው ሳይሆ ን ገዳዩ ብቻ ነው:: ጊዜ ካለፈ በኋላ፤ ትግሉ ተፋፍሞ ባለበት ጊዜ እግሬ አውጪኝ ካሉት ብዙ ጊዜ የሚሰሙ ትችቶች በመሰረቱ ፍሬቢስና ገበናን ወይም ድክመትን መደበቂያ ናቸው:: በሙሶሊኒ ጣሊያን ወረራ ጊዜ አርበኞች ያን ግዙፍ ጠላት መጋፈጣቸው፤ ታንክን በጦርና በቼከ ዝ ጓንዴ ሊመልሱ መነሳታቸው ስህተት ነው ብለው ዛሬ የሚተቹ አሉ፤ ያኔም አሜሪካኖችና

እንግሊዞች ተሳልቀው ነበር፡፡ አርበኞች ግን ጠላት ሀያል ነውና እጅ እንስጥ ወይም ባዕዳን መጥ ተው ነፃ ያውጡን ብለው አልጠበቁም፡፡ ባላቸው ብረትና አቅም ተነስተው ጠላትን ተጋፈጡት እንጂ፡፡አፄ ኃይለሥላሴ ሀገር ጥለው ሲወጡም ተቃዋሙ እንጂ እሰየው አላሉም--ንጉስና መሪ በግንባር ተገኝቶ ትግሉን እንዲመራ ይጠበቃል እንጂ፡፡ ቴዎድሮስ ተባለ ዮሐንስ ወይም ምኒሊ ክ የታየውፍርጠጣ አልነበረም--ግና አፄው የሰረዙትን ታሪክ ነፍሰ ገዳዩም ኮለኔል ተቀብሎ ውር ደትን ተከናናበ ፡፡ ነገም ለመለስ ከሆነለት የሚጠበቅ የቡከን መጨረሻ ነው--ፍርጠጣ! ጣሊያንን ሲቃወምና ሲታገል ከሚሊዮን ያላነሰ ዜጋ አልቋል፡፡ የአርበኞች ጥፋትም አልነበር፡፡ በዘመነ ደርግም ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ያ ትውልድ ከፍሏል--አኩሪና ዘወትር የምንኮራበት ታሪክ ነው፡፡ በየእስር ቤቱ ስየል የተቀበሉትና ብዙ መከራ ያዩት ሁሉ ሀገር የምትኮራባቸው ናቸው፡፡ በባንዳውና ነፍሰ ገዳዩ እንደምታፍረው ሁሉ፡፡

ፀረ ወያኔው ትግልም ቢሆን ከደረጃ ወደ ደረጃ ከፍ እያለ በመምጣት ላይ ነውና የሀሰት ዘማቾች ን መቋቋም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ለማስወገድ ሀገር ወዳዱ ሁሉ የደም ዋጋ መክፈል አለበት፡፡ ይህ አረመኔ አገዛዝ በምለላና በሰላም የሚወገድ አይደለምና፡፡ 19 ዓመት ሙሉ ያየነውንና የደረሰብንን ሁሉ ካልካድን በስተቀር ዛሬ የመለስ ቡድን አለመራራ ትግል ይወድቃል ብሎ መደምደም “ እግዚኦ ጅልነት ወይም ሽንፈተኛነት ያብቃ” የሚያሰኝ ነው፡፡ ይልቁንስ የውሸት ነገሮችን ከበሮ ድለቃ ጆሮ አንሰጥ ብለን ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል በቆራጥነት መዘጋጀት መነሳት ይኖርብናል፡፡ ይህን በዚህ ትተን ወደሚነዙት ውሸቶች ስንመለስ ደግሞ ደጋግመን እንዳልነው ሀቁ የነበረው ስርዓት በኢሕአፓ ላይ ፍጅት ማወጁንና ግደያ መጀመሩን ያረጋግጣል፡፡ በ1983ም ቢሆን ኢሕአፓ ጦረኛ ሆኖ ለሰላማዊ ትግል እምቢኝ ያለ ሳይሆን የወያኔ አገዛዝ ኢሕአፓንም ሆነ በኢዴኃቅ የተሰባሰቡትን ሁሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከተከበሩ በሰላም ሊታገሉ ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀው እያለ ወያኔም ያኔም ሆነ ከዚያ ም በኋላ አሻፈረኝ ማለቱ ሀቅ ነው፡፡ ደርጉ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት ሲያውጅ ኢሕአፓ የራስ መከ ላከል እርምጃን መውሰድ ተገዶ በከተሞችም ጥይት ተኩሷል፡፡ ይህ ተገቢና ዛሬም ቢሆን ትክክለ ኛ እርምጃ ነው የምንለው ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ኢሕአፓ ራሱን ገምግሞ ባካሄደው ግለሂስ ለሰማዕቱ ሁሉ አከብሮቱን እየገለፀ ግን የተወሰኑ ስህተትን መፈፀሙን ደግሞ አምኗል፡፡ ሀቁ ሲነገ ር ኢሕአፓ መቸም ቢሆን መች በከተማ በሚደረግ ተኩስ አገዛዙን ማሸነፍ ይቻላል የሚል አቅዋ ም አልነበረውም፡፡ በገጠር መሰረቱን ባደረገ ሕዝባዊ ጦርነት መሰረት ነው ድል የሚገኘው የሚል ነበር የኢሕአፓ አቅዋም፡፡ ሆኖም ግን በራስ መከላከል አቅዋም መሰረት የተወሰነው ቀስ በቀስ እየሰፋ የድርጅቱ ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ዘርፎችም የየራሳቸውን ስኳድ እየመሰረቱ እንዲሰማሩ መደረጉ ድርጅቱ ላይ ጉዳትን ማስከተሉ አልቀረም፡፡ ይህን ሁሉ ድርጅቱ ራሱ ከዓመታት በፊት ገምግሞ የጨረሰው ጉዳይ ነው፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ማለትም በከተማ የነበሩ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በመሰዋታቸው ( ለምሳሌ ክፍሉ ከበደ ፤ ዮሐንስ ብርሃኔ፤ ዮሴፍ አዳነ ፤ ተስፋዬ ደበሳይ) ወይም ወደ አሲምባ በመዛወራቸው (ለምሳሌ ፀሎተ ሕዝቅያስ፤ ዘሩ ክህሸን)ና ወደ ውጭ ለስራ በመላካቸው (አ.ዋ. ለምሳሌ) ፤ ሁለቱ አንጃ በመሆናቸውና ድርጅቱን በመልቀቃቸው (ብርሃነ

መሰቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ) አንድ የአመራር ግለሰብ ብቻ በከተማ በመቆየቱና ይባስ ብሎም ከአሲምባ ይላኩ የነበሩ ውሳኔዎችን ባለማክበሩም ብዙ ስህተት ተፈፅሟል፣ ጉዳት ደርሷል:: ይህን ስህተት ሁሉ ድርጅቱና በተለይም ማዕከላዊ ኮሚቴው የራሴ ነው ብሎ በሀላፊነት ተቀብሎ ግለሂስ ቢያደርግም ሀቁ ግን እንደተጠቀሰው በአብዛኛው አንድ ግለሰብን የሚመለከት ነበርም ማለት ይቻላል:: ኢሕአፓ በከተማ ራሱንና ሕዝብን ለመካላከል ባለው አቅም ሁሉ መጣሩና አስፈላጊውን መስዋዕትነትንም በመክፈሉ አጠፋሁ የሚለው የለም--ሰማዕቱን ይዘክራል፣ መከራ የተቀበሉትንም ያከብራል እንጂ:: በስህተት ደረጃ ግን ይህ የመከላከል እርምጃ ተስፋፍቶ ወደ ከተማ ትጥቀ ትግል ሊያድግ መቃጣቱ፣ ፖለቲካዊና የትጥቅ መዋቅሩ መደበላለቁ፣ ዴሞክራሲያ ዊ ግንባር በሚልም ምስጢራዊ መዋቅሩን ሊያስጠቃ በሚችል ደረጃ ምልመላ መካሄዱና የሕዋስ አሰራርና የመዋቅር አለመቆላለፍ መርህ መጣሱ በየፈርጁ ጉዳትን አባብሷል:: በተለይም የሀይል ሚዛኑ ወደ ደርግ ማድላቱ ግልፅ ሆኖ ሲመጣ (የኩባ፣ደቡብ የመንና የሶቭየት ህብረት ካምፕ ሁሉ ከጎኑ ሲቆሙና የአረመኔው መንግሥቱ የበላይነት በደርግ ውስጥ ሲረጋገጥ) የከተማውን ትጥቃዊ እንቅስቃሴ ማቆም ሲገባ ይቁም ሲባልም በመቀጠሉ ስህተት ተፈፅሟል:: በድርጅቱ ውስጥ የተከሰተው አንጃም ያደረሰው ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም:: ይህ ሁሉ መባሉ አንድም ድርጅቱ ራሱን አልገመገመ ለሚሉት ውሸታቸውን ለማጋለጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሚታገል ድርጅት ስህተት መፈፀሙ አስገረሚ አለመሆኑን ለማስጨበጥም ነው:: ቁምነገሩ ስህተ ት እፈፅማለሁ ብሎ ከድርጊትና ትግል መታቀብ ሳይሆን ስህተተን ላለመድገም ጥንቃቄ ማድረጉ ላይ ነው:: የኢሕአፓ አባላት ለሀገርና ለሕዝብ ሲሉ መሰዋታቸውና መከራ መቀባላቸው የሀገራች ን አኩሪ ታሪክ አካል ሆኖ በትውልድ የሚዘከር መሆኑን ግን የማንም የውሸት ዘመቻ የሚያግደ ው ወይም የሚያስቀረው አይደለም::

ወደ ችግሮችና ክፍፍልም ስንመጣ ውሸት አይታክቴዎቹ ነጋ ጠባ እንደሚሉት ሳይሆን ሀቁ ግን የትግል ውስብስብነትና ይህም ህይወቱ ለትግል ያሉ ግለሰቦችንም ሳይቀር ጫና እንደሚያደርግባ ቸው የሚያሳይ ነው:: ቀደም ብለን በመደጋገም ልናስረዳ እንደሞክርነው ኢሕአፓ ለስልጣን ይታገላል ካሉ በኋላ ይህንን በክስ መልክ ሊያቀርቡ ለሚሞክሩት ያለን የሁልጊዜ መልስ በተለመ ደው አነጋገር ታዲያ ምን ይጠበስ ትግላችን ለስልጣን ነውና የሚል ነው:: ግና ኢሕአፓ ስልጣን ሲልና ሌሎች ስልጣን ሲሉ የተለየ ጉዳይ ነው--ለኢሕአፓ ትግላችን ለፖለቲካ ስልጣን ነው ሲል ለሕዝባዊ ስልጣንና ለሀገር ሉዓላዊነት ማለቱ ነው:: የሕዝብ መብት ለሚከበርበት ስርዓት፣ በነፃ ምርጫ ሕዝብ መንግስቱን ለሚመሰረትበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማለቱ ነው:: የኢሕአፓ መሪ ዎች ለስልጣን የሚበቁበት ማለት ቢሆን ኖሮ ከደርግም ከወያኔም ጋር የስማምቶና በርከክም ብሎ ሹመትን በተቀራመተና በሕዝብ ላይ በተወዘፈ ነበር:: በኢሕአፓ የተፈጠሩት አንጃዎች ሁሉ -የያኔውም የዛሬዎቹም--ጋር ቢሆን ድርጅቱ ያለው መሰረታዊ ጠብ የፖለቲካ እቅዋምን ይመለከታል:: የቀድሞዎቹ ከደርግ ጋር አብረን እንስራ ሲሉ የዛሬዎቹ ደግሞ ለወያኔ እንጎንበስ በማለታቸው ልዩነት ተፈጠረ እንጂ ጠቡ የግለሰቦች አይደለም:: አንዳንድ ቀጣፊዎችና ጥራዝ ነጠቆች ለምሳሌ ኢሕአፓም ሆነ ደርግና መኢሶን አቅዋማቸው አንድ ነበር--በስልጣን ተጣሉ

ይላሉ፡፡ ይህ ግን ሀሰት ነው፡፡ ከደርግ ጠቡ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሰት እንዳይቋቋም ጋሬጣ በመሆ
ኑና ወታደራዊ አምባገነንነትን ለማስፈን በመነሳቱ ነው፡፡ ከመኢሶን ልዩነቱ እነሱ ደርግን ደግፈን
ና በሂስ አጅበን አብረነው በስሩ እንስራ ሲሉ ኢሕአፓ ደግሞ ደርግ ቦታውን ለቆ ጊዜያዊ ሕዝባ
ዊ መንግስት ይመስረት በማለቱ ነው፡፡ ሌላው ሁሉ ትርፍ ነበር፡፡ ዛሬም ከዘመናዊ ባንዶችና አንጃ
ዎች የሚለየው እነሱ ከወያኔ ጋር በይፋ ወይም በሽፍንፍን ተለጣፊነት እንስራ ሲሉ ኢሕአፓ
ወያኔ በህዝባዊ ትግ መወገድ ያለበት ፀረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ ነው በማለቱ ነው፡፡ የሚታ
ረቅ አቅዋም አለመሆኑ ግልፅ ነው-- ኢሕአፓ መቸም ቢሆን መቼ ሕዝብን ሀገርን ክዶ ለወያኔ
አያድርምና፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ኢሕአፓ ስለ ድርጅትና መርህ ያለውንም አመለካከትና አቅዋ
ም  መጥቀሱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህ አቅዋሙ የማይገባቸው ደግሞ ድርጅቱን በአክራሪነት፣
በግትርነት፣ በተንኳሽነት ወዘተ ሊከሱና የሀሰት ክስ ሊጭኑበት የሚዳክሩ ጥቂቶች አይደሉም፡፡
መሰረትና ሀቅ የላቸውም፡፡

ኢሕአፓ ሀ ብሎ ትገል ሲጀምር ቃል ኪዳኑ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ነው፡፡ ሀገራችን ተበደለች፣
ተጎዳች፣ ሕዝቧም ተበዘበዘ መከራው በዛ፣ መብቱ ተረገጠ እኩልነትና ዴሞክራሲን አጣ ብሎ ይህ
ን ሁኔታ ለማስወገድና፣ የሕዝብ ወሳኝነትንና የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር ብሎ አመፀ ታገለ
እንጂ ማንንም አገዛዝ ሆነ ግለሰብ ለማስደሰት ሆነ ከማንም ጋር ተሞዳምዶ ቃል ኪዳኑን ለመሸር
ሸርና ለመሻር አልነበረም፣ አይደለም፡፡ ለኢሕአፓና አባሎቹ መርህ ማለት ክታብ-- እምነት
ነው--ቃሉ ክቡር ነው፡፡ የግለሰቦች ሀሳባቸውንና አቅዋማቸው የመቀየር መብት የተጠበቀ ቢሆን
ም ዛሬ  የሰላ የድርጅት ቱሪስት የሆኑ ብዙ አሉ፡፡ ይህ የሀሳብ የመቀየር ችሎታን ሳይሆን የሚያ
መለክተው መርህ ማጣትን ወይም መርህን አለማክበርንና ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባልን
ነው፡፡ ይህን ዓይነት ከዚህ ከዚያ ማደርና በሞቀበት ሁሉ መጣድ ልምድ ያላቸው ሁሉ ኢሕአፓን
በግትርነት ቢከሱት የሚገርም አይሆንም፡፡ ንፁህ አድርባይነት በሚገባ ሲመረመር በጣም ቆሻሻ
ነው፡፡ ኢሕአፓ እነዚህን መርህ ብሎ ያነገባቸውንና መስዋዕትነት የከፈለባቸውን ዛሬም ክቡር
ብሎ ይዞ ያለው ግትር ሆኖ ሳይሆን ዛሬም የሕዝብ መሰረታዊ ጥያቄ ቅንጣትም ተገቢውን ምላሽ
ባለማግኘቱ ነው፡፡ መሬት ለአራሹ፣ ዴሞክራሲ አለገደብ፣ ሉዓላዊነቷ የተከበረ ሀገር፣ እኩልነት፣
የላባደሩና ሰርቶ አደሩ ሕዝብ በአጠቃላይ መብት መከበር ወዘተ ገና የመልስ ያለህ እያሉ ናቸው
፡ይህ ሀቅ ሆኖ ባለበት አቅዋምን እያሸጋሸጉና ለመጣው ባለነፍጥ እያደሩ የግል ጥቅምን ማደለብ
የኢሕአፓ አቅዋም ሆኖ አያውቅም፣ የሚሆንም አይደለም፡፡ ብልህ ሆንን፣ ስልጡኑን ፖለቲካ
ተረዳን፣ መርህ ብሎ መድረቁ ያለፈበት ፖለቲካ ነው፣ ዶክተሮቹና አዋቂዎቹ ወይም ማለት
እንደሚወዱት ልሂቆቹ እኛ ነን ወዘተ ወዘተ በሚል ከሕዘብ ጠላት ጋር መሞዳሞድን የሚሰብኩ
ትን ኢሕአፓ ግትር ብሎ ዛሬም የሚታገላቸው ነውና ሀሰት ቢረጩበት ብዙም የሚገርም አይሆን
ም፡፡ ትግል ስንል መርህና ሕዝባዊ ዓላማን ማስቀደም ነው፡፡ የሕዝብን ጥቅምና የነፃነት ፍላጎት
የሚፃረረውን ሁሉ በባህል ወይም ወግ ሽፋን ኢሕአፓ አይቀበልም፡፡ ባህላችን ነው በሚል ጎጂ ባህ
ሎችን፣ ፀረ ሴት ልምዶችን፣ ሕዝብን ከፋፋይ አቅዋሞችን፣ ትምክህትና ጥበትን አያስተናግድም፡
ለኢትዮጵያና ለሕዝብ ቆመናል፣ ለውጥ ፈላጊ ነን እያሉ ተመልሰው ወደ ቀድሞው መወገድ

ወዳለበት እምነትና ልምድ ወይም አቅዋም የሚገቡትን--ጎጠኛና ዘረኛ ወይም በሀይማኖት መሰረ ት አክራሪና ግጭትን ጋባዥ የሚሆኑትን--ኢሕአፓ ይቃወማል:: ግለሰቦችን በጣዖትነት ማስቀመ ጥ ደግሞ ከድርጅቱ መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊና እኩልነት፣ የሕዝብ ወሳኝነት አቅዋም ጋር የሚፃ ረር በመሆኑ መቸም ተቀብሎት አያውቅም:: በድርጅቱ ውስጥ የጋራ አመራርና ሀላፊነት፣ህቡዓዊ ነት የሚፈቅደውም ዴሞክራሲ የሰፈነ በመሆኑ በአምባገነንነት ወይም በአምልኩን ባይነት ብቅ ያሉትንም ግብዞች ለማረም ሞክሮ አልሰማ ሲሉ በተርታ አስወግዷቸዋል:: ኢሕአፓ አቅዋም የሚወስደው በመርህ መሰረት በመሆኑ ልዩነትም አቅዋሞቹም ሁሉ ሊገመቱ የሚችሉት ከዚህ በመነሳት ነው:: ዋሾዎች ሲሉ እንደሚደመጡት በኢሕአፓ ሁሉን ወሳኝ ግለሰቦች፣ አምባገነን እገሌዎች የሉም፣ ሊሆኑ የሞከሩ ተሸኝተው ውድቀትን ተከናንበዋል:: ኢሕአፓ እምነቱና ማንነ ቱ አንድ መሆን አለባቸው ብሎ ያምናል:: በመርህ መሰረት መኖርና መርህና እምነትን ህይወትን ገላጭ ማድረግ በጣም ከባድ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: በዘልማድ ብዙዎች የሚቀናቸው በዝምደና ሆነ በጓደኝነት፣ በጥቅም ሆነ በፍርሀት አድርባይ መሆን ነው:: ጋሼ ይቀየማልና አቅዋም አልይዝ ም፣ እገሌ ትግል በቃኝ ካለ እኔ ማን ሆኜ ነው የምቀጥለው፣ አብሮ አደጌ ጋር እስለፋለሁ፣ በአቅ ዋሚከፀናሁ ከወዳጆቼ እለያለሁ፣ እስከመቼ ትግል እነ እገሌ ሲንደላቀቁ እያየሁ፣ሕዝብ የራሱ ጉዳይ ሁሉም ለየራሱ ወዘተ በሚል ተገቢውን አቅዋም መያዝና ፀንቶ መቆየት የሚያቅታቸው ጥቂቶች አልነበሩም፣አይደሉም:: ድክመታቸውንም ለመሸፈን በኢሕአፓ ላይ የሀሰት ክሶችን መደርደርና አሉባልታዎችንም ማሰራጨት ላይ ተሰማርተው አይተናል፣አድምጠናል:: ከድክመ ታቸው የተነሳም ጥርትና ቁርጥ ያለ ወገንተኛ አቅዋም የመያዙ ይሳናቸውና ሲወላውሉ ወይም ወግድ ማለት የሚገባቸውን ጠላት፥ አድርባይና ባንዳ ሲያቅፉ ወይም ሊያስተናግዱ ሲቃጡ ይታያሉ:: ኢሕአፓም በዚህ ጎዳና ስለማይጓዝ አክራሪ ብለው በውሸት ሊያወግዙት ይሮጣሉ:: ኢሕአፓ ድርጅትና የድርጅት መሪዎችም የሕዝብ አገልጋይ እንጂ ከሕዝብ በላይ አይደሉም ብሎ ስለሚያምን ጣዖት ፈላጊዎች ፀረ ድርጅቶች ነው ብለው በሀሰት ይከሱታል:: የድርጅት መሪዎች እንደአኤው ስልጣናቸው የማይጠየቅና የማይገሰስ ነው ይባልናም ገና ሳይፈተኑ ማንዴላ ወይ ሌላ የሚል ቅፅል ይለጠፍባቸውና ቆጥ ስለሚሰቀሉ ነገሮችን ሲያባላሹና የሕዝብንና የሀገርን ም ጥቅም ሲጎዱ እንኳን መተቸት ከማይቻልበት ደረጃ ይደርሳሉ:: ኢሕአፓ ይህን መቸም የሚቀበል አይደለምና የሕዝብ መሪ ነን ብለው ራሳቸውን የሰየሙትን ወይም ጫጫታ በሚቀናቸ ው ሳይታገሉ " ዕድሜ ልክ የታገሉ " ተብለው የሚሞገሱትን፣በጀግንነት ተግባር ከቶም ሳይታዩ ጀግና የሚባሉትንም በተመለከተ ጎበዝ አደብ አንግዛ አንጂ፥ ነገር አይበላሽ እንጂ ብሎ ኢሕአፓ ማሳሰቢያና አርምት ሲሰነዝርም በክብረ ነክ ያወግዙታል:: ሀቁን በመናገር መወገዝ ይሏል ይህ ነው:: ከዚህ ባሻገር ግን ኢሕአፓ ያለውን አረመኔ አገዛዝ መታገልን ቅድሚያ በመስጠቱ የስንቱን ገበና ለስንቱ ደብቆላቸው እንዳለ የሚታወቅ ነው ማለትም እንችላለን:: ለማንኛውም በኢሕአፓ ሀቀኛ አባላት ቅድሚያ የሚሰጠው ለሀገርና ለሕዝብ በመሆኑ በአጓጉል ይሉኝታ፣ የመንደርና የጎጥ ልጅነት፣ መሰረት ቢስ መቻቻል ወይ መሰል አልባሌና መወገድ ባለባቸው የተሳሳቱ አቅዋሞ ች የተነሳ ቃልኪዳንና መርህን የሚያፈርስ መሞዳሞድ መቼም የሚታይ አይሆንም:: ይህን አሌ ያሉትና ለጠላትም ፈካ ጎንበስ ለሊሉ የቃጠትንም ከመሀሉ አውጥቶ ወደሚሄዱበት ሂዱ ብሎ

በተደጋጋሚ ሸኝቷል።

ኢሕአፓ በሀገር የሚኮራ ነውናም የጀግና ምሳሌ ፍለጋ በየባዕድ ሀገር መባዘኑን በበጎ አላየውም።
ወር የታሰረውን ማንዴላ አትበሉ፤ በእስር የሚሰቃዩ ምሳሌዎች ከፈለጋችሁም የእኛዎቹ የሀገራች
ን ሞልተዋልና ምነው ባዕድ ሀገር ምሳሌ ፍለጋ መሄድ ተገደዳችሁ ይላል። የጀግና ምሳሌም
ለአረመኔ አገዛዝ ያደሩ ሳይሆኑ ለሕዝብ ሲሉ ህይወታቸውን የገበሩ መሆን አለባቸው ሲል ደግሞ
ደጋግሞ አሳስቧል። ለጀግና ደግሞ አያሌ የጀግና ምሳሌ ያፈራች ሀገር ናት ኢትዮጵያ። አንገታ
ቸውን ለሰይፍ፤ ደረታቸውን ለጥይት፤ አንገታቸውን ለገመድ የሰጡ አያሌ ጀግኖች ነበሩ አሉም፡
፡ ትላንት ስንቱ በትግል ሲሰዋና ሲሰቃይ ለአገዛዙ ሲሰግድ፤ ሲያገለገል ወይም ሲዘፍን የነበረውን
ሁሉ ጀግና ብሎ ጀግና የጠፋ ይመስል ቡራ ከረዩ ማሰማት አሳፋሪ ነው። ይህን በማለቱ ኢሕአፓ
የሚወገዘው ለምን ይሆን? እውነትን በተናገረ ? ራሳችንን ታሪካችንን እናክብር ባለ? በሰማዕት
ደም አንቀልድ ባለ? አስመሳዩን ከሀቀኛው ሀገር ወዳድ አናደባልቅ ባለ? አታላይ ለጊዜው ያመል
ጣል፤ በኋላ ይሰምጣል የተባለውስ ለምን ይዘነጋል?

ከዚህ በፊት እንደተባለው ኢሕአፓ በቅደሚያ ተጠያቂነቱ ለሕዝብና በሕዝብ ነው ። ለወንጀለኞ
ች፤ ቀይ ሽብርተኞችና ወያኔዎች የሚሰጠው ምላሽ ወይም ተጠያቂነት የለም። ዛሬ የኢየሱስን
ቤት ወራሽ ነኝ ብሎ እንባ የሚረጨው ታምራት ላይኔ በ1983 የኢሕፓ ወራሽ እኛ ኢሕዴኖች
ነን ብሎ ለፍፎ ነበር። ከወያኔ ጋር አብሮ ኢሕአፓን ወግቶ የገደለና የጨረሰ መስሎት ሊወርስ
ቃጥቶት ነበር--ግን ኢሕአፓ ያኔም ቢሆን ማን ቢወልድ ማ ብሎ ምላሹን ሰጥቶታል። የኢሕአ
ፓ ባለቤት ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያ ሰፊው ጭቁን ሕዝብ ነው። የኢሕአፓ ባለቤቶች ዛሬም ቢሆ
ን ኢሕአፓ ሆነው የሚታገሉት እባሎቹ ናቸው። ከዕለታተ አንድ ቀን ኢሕአፓ ነበርን ተረት
ተረት ባዮችና ዛሬ የጠላት ሎሌዎች የሆኑት ኢሕአፓ አይደሉም። በመሆኑም በነበርን ደረጃ
ሊደረደሩ የሚሞክሩት ውሸትና ክስ ሁሉ ዋጋ ቢስና መሰረት ቢስ ነው። ለነገሩ ብዙዎቹ በድርጅ
ቱ እምብዛም አልቆዩምና፤ በውስጡ በተጨባጭ ትግል ተሳትፈው ይህ ነው የሚባል ተመክሮ
አላገኙምና ገባ ወጣቸው ኢሕአፓ ስለማያደርጋቸው ለውሸታቸውና ዝቅጠታቸው ሁሉ
ኢሕአፓ ተጠያቂ አይሆንም። የቆዩና ውሎ አድሮ ደግሞ ቃል ኪዳናቸውን ያፈረሱ ደግሞ ቆቡ
ን ያወለቀ፤ጥምጥሙን የፈታ ቄስ ዓይነት ናቸው--ወጥተዋልና የሉበትም። ስለ ኢሕአፓ የመናገ
ር ወይም ኢሕአፓ ነን ብሎ የመናገርም መብታቸው አክትሟል ማለት ነው። በኢሕአፓ ላይ
የሀሰት ዘመቻ ከፍተው ይህንኑ ለማሳመን ኢሕአፓ ነበርን የሚሉትን የነበርን መራሾች ሕዝብ
ጆሮ ሊሰጣቸው አይገባም።

በኢሕአፓ ላይ የውሸት ዘመቻው የሚቀንስ ሳይሆን የሚባባስና የሚስፋፋ መሆኑን ከወዲሁ
መተንበይ ይቻላል። የኢሕአፓ ፀረ ወያኔ ትግል በደረጃ እያደገና እየተጠናከረ መምጣቱ እየታየ
ያለ ነው። ኢሕአፓ ሕዝበን ሊያደናግሩ የሚጥሩትንም ሳይታክት እያጋለጠ የሕዝብን ትግል
እየተከላከለ ነውናም አወናባጆቹም ይረባረቡበታል። ይህ ሁሉ የሐሰት ዘመቻ ግን የሚያሳየው

ኢሕአፓ ዛሬም ፀረ ኢትዮጵያ ሀይሎችና ፀረ ሕዝቦችን ሁሉ አምርሮ እየታገለና እያሰጨነቃቸው መሆኑን ነው። የሕዝብ ጠላቶችም ይዋሻሉ፤ ኢሕአፓም ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥላል። ውሸት የማይቀይረው ሀቁ ይህ ነው።

ያ ትወልድ ይዘምር እንደነበረውም፤

በትግል የሚሞቱ አቸናፊ ናቸው
በትግል የሚኖሩ አቸናፊ ናቸው
ጭቆና ባለበት ሞገድ እያስነሳ
የታጋይ ድምፁ ይጮኻል ይጣራል
ይላል አሁኑኑ
እናምፅ አምፁ ።

ይቀጥላል